ለበለጠ ዝርዝር ትኩረት በ2004 የዓለም አቀፋዊ የሃይማኖት ነፃነት ዘገባን ይመልከቱ።

መ/ በአገሪቱ ወስጥ በነፃ ስለመንቀሳቀስ፣ የውጭ ጉዞ፣ መሰደድ፣ እና መመለስ ሕገ መንግሥቱ እነዚህን መብቶች መከበር የደነገገ ቢሆንም፣ መንግሥት ከእነዚህ መብቶች አንዳንዶቹን በግብር አጣብቧል/ተቆጣጥሯል።

በዓመቱ ወስጥ በሙለ፣ ወደ ጋምቤላ ክልል በሚገባ የችግር ማቃለያ ዕርዳታ አቅርቦት እና በሰብዓዊ ድርጅቶች ወደ ሥፍራው ለመድረስ የሚያደርጉትን ጉዞ መንግሥት ቾቄቄሀ ቁልዎማኝ ይከታተል እና አንዳንድ ጊዜም ይቆጠጠር ነበር፣ ይህን የሚፈጸመውም ወደ ሥፍራው መሄድ ለሚያቅዱ ወገኖች ደህንነት እና ለሕይወታቸው ጥንቃቄ ማድረግ በማስፈለጉ መሆኑን ገልጿል። በታኅሣሥ 3/96 ከደረሰው አደጋ ቀጥሎ፣ ለተወሰነ ጊዜ ጉዞም ተቋርጦ ነበር።

ከአገሪቱ ከመውጣት በፊት ዜጐችና ነዋሪዎች የመውጫ ቪዛ እንዲኖራቸው የሚያስገድደው ሕግ ከሐምሌ ጀምሮ ተሰርዟል። ኤርትራውያንና የኤርትራ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ሁኔታ መንግሥት መስመር አስይዞታል።

ከአገር ማጋዝ ክልክል ነው፣ በዓመቱ ወሰጥ በግድ ከአገር ስለተጋዙ ሰዎች ዘገባዎችም አልነበሩም። 54 ጋዜጠኞችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች በእራሳቸው ምርጫ እንደተጋዙ ይገኛሉ (ክፍል 2 ሀን ይመልከቱ)።

በ1996 ዓ.ም ወደ ኤርትራ መመለስ የሚፈልጉ 1579 ኤራትራውያን ሰላማዊ ሰዎች በቀይ መስቀል ዓለም አቀፋዊ ኮሚቴ እጅ በአገሪቱ ውስጥ ይገኙ ነበር። በዓመቱ ውስጥ የቀይ መስቀል ዓለም አቀፋዊ ኮሚቲ ያስተናገዳቸው በርካታ ወደ አገር የመመለስ አጋጣሚዎች ነበሩ። አብዛኞቹ ኤርትራውያንና የኤርትራ ተወላጅ የሆኑ ኢትዮጵያውያን መንግሥት ዘንድ ተመዝግበው በሆስፒታሎች እና ሕዝባዊ አገልግሎቶች መጠቀም የሚፈቅድላቸው እና ለ6 ወራት የሚያገልግል መታወቂያ ነበራቸው። ሆኖም፣ በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የኤርትራ ተወላጆች የሆኑትን ነፃ የሕክምና አገልግሎቶችን፣ ይከለክሉዋቸው እንደነበረ የሚያምኑ ያልተረጋገጡ እና በገጠመኞች ላይ የተመሠረቱ ዘገባዎች ነበሩ።

በ1994 ዓ.ም. መንግሥት ቢያንስ 200 ከሠራዊቱ የከዱ እና በዲዬሳ ማገቻ ማዕከል ተይዘው የነበሩ ኤርትራውያንን በሰሜን ወደ እሚገኘው የስደተኞች ሰፈር አዛውሯል። የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽነር (የመሰከኮ) የ178 ቱን ሁኔታ በ1994፣ የ94ቱን በዓመቱ ውስጥ አጣርቶ እንደገና ለሚቋቋሙባቸው ሶስተኛ አገሮች አዘጋጅቷቸዋል። በዓመቱ መጨረሻ ሌሎች ያላለቀላቸው ተመሳሳይ ጉዳዮች መኖራቸው አልታወቀም። ከ1990 ዓ.ም. እስከ 1992 ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት የተነሳ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለአገር ወስጥ ተፈናቃይነት ተዳርገዋል። በጦርነቱ የተነሳ ከተፈጠሩት 350,000 ያህል የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች 225,000 ያህል የሚሆኑት መልሰው ተቋቁመዋል።

በተለያዩ ጐሣዎች መካከል በተፈጠሩት የከረሩ ግጭቶች ምክንያት በዓመቱ ውስጥ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል፣ ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ወይም ለአገር ውስጥ ተፈናቃይነት ተዳርገዋል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)።

ሕጉ የስደተኞችን አቋም በሚመለከት በ1943 ዓ.ም. በተደረገው የተመድ ስምምነት (ኮንቬንሽን) ወይም በ1959 ዓ.ም. ፕሮቶኮል መሠረት ለስደተኞች ጥገኝነት እንዲሰጥ ይደነግጋል። መንግሥትም ይህ ጥበቃ እንዲሰጥ የሚያደርግ ሥርዓት አቋቁሟል። በዓመቱ ወስጥ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብሔራዊ የስደተኛ ሕግ አጽድቋል። ነገር ግን ሕጉ በነጋሪት ጋዜጣ ስላልታተመ አልጸናም። በግብር መንግሥት በጠቅላላው ስደተኞች ዳግም በደል እንዳይደርስባቸው፣ ሰዎች እንጨቆናለን ብለው ወደ እሚፈሩት አገር እንዳይመለሱ ጥበቃ በማድረግ የስደተኛ አቋም ወይም ጥገኝነት ይሰጣል። በአጠቃላይ መንግሥቱ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (የተመሰከኮ) እና ከሌሎችም የሰብዓዊነት ድርጅቶች ጋር ስደተኞችን እና ተመላሽ ዜጐችን በመርዳት ይተባበራል።

የስደተኞች ቁጥር በ1995 ዓ.ም. ከነበረው 128,610 ዝቅ ብሎ ከመሰከረም ጀምሮ አገሪቱ 121000 ያህል የሚሆኑ ስደተኞችን ታስተናግዳለች። ከእነዚህ ውስጥ 89,000 ያህል የሱዳን ስደተኞች በ5 የስደተኞች ሰፈር በምዕራብ ነበሩ። ወደ አገር የመመለስ ፕሮግራም ቀጥሎ ስለነበረ በምሥራቅ የስደተኛ ሰፈሮች የሚገኙት የሱማሊያ ስደተኞች ቁጥር በ2 ሰፈሮች፣ አይሻ እና ቀብሪ ቢያ፣ ወደ 23,000 ያህል ዝቅ ብሏል።

የሃርቲሼክ ሰፈር በሐምሌ ተዘግቷል። መንግሥት ከተመሰከኮ ጋር በመተባበር ከሱዳን እና ሶማሊያ ለመጡ ስደተኞች ጊዜያዊ ጥበቃ አድርጓል።

በዓመቱ መጨረሻ 24500 ያህል የኑዌር እና የዲንካ ስደተኞች በፋኘንዶ ሰፈር፣ ጋምቤላ ክልል ነበሩ። በታኅሣሥ 1995 ዓ.ም. ያልተወቁ አጥቂዎች፣ / እንደሚባለው ግን የአካባቢው አኙዋክ ተወላጆች፣/ የመንግሥት የስደተኛ ሹሞችን በሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ ላይ ጥቃት በማድረስ ስምንት ሰዎችን ከገደሉ በኋላ፣ የኑዌር እና የዲንካ ስደተኞችን ከፋኘንዶ ሰፈር የማዛወር ዕቅዶች ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፈዋል። ሹሞቹ በአዲየ ቦል ወስጥ ወደ ታሰበው አዲስ ሰፈር በመሄድ ላይ ነበሩ (ክፍል 5ን ይመልከቱ)።

በግንቦት ወር የኤርትራ ስደተኞች ከዋአላ ንሂቢ ጊዜያዊ ሰፈር ከድንበሩ ራቅ ወዳለ አዲስ ቋሚ የስደተኞች ሰፈር ተዛውረው ነበር። አዲሱ ሰፈር፣ ሺሜልባ 8,200 ያህል የኤርትራ ስደተኞችን የያዘ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 4,200 የሚሆኑት በነገድ ኤርትራውያን ኩናማ ናቸው። በሺሜልባ ሰፈር የነበረው የጤና፣ የትምህርት፣ የውሀ እና የንጽሕና አገልግሎት እምብዛም ነበር።

በጋምቤላ ክልል በተለያዩ የነገድ ስብስቦች መካከል የተፈጠረው ግጭት የተመሰከኮን ስደተኞችን የመጠበቅ ጥረት ወስብስብ አድርጐታል (ክፍል 5ን ይመልከቱ)። በምዕራብ በኩል ውጥረት ቢኖርም፣ ለስደተኞች ምግብ ማድረሱ እንደቀጠለ ነበር። ሆኖም፣ በነበረው የመጓጓዝ ቁጥጥር እና መጣበብ ምክንያት የሰብዓዊ ድርጅቶች ምግብ የማድረሱን ሥራ በሚገባው ያህል መከታተል አልቻሉም።

በዓመቱ መጀመሪያ ላይ እጥረት የነበረባቸውን ነገሮች በሚመለከት በአካባቢው ነዋሪዎች እና በስደተኞች መካከል ግጭት ስለመፈጠሩ ያልተረጋገጡ ዘገባዎች ነበሩ።

ክፍል 3 የፖሊቲካ መብቶችን ስለ ማክበር፣ ዜጐች መንግሥታቸውን ለመለወጥ ያላቸው መብት

ዜጐች መንግሥታቸውን በሰላም የመለወጥ መብት ያላቸው መሆኑን ሕገ መንግሥቱ ደንግጓል። በ1992 ዓ.ም. በአብዛኛው አካባቢዎች ነፃ እና ፍትሐዊ ሆነው በተካሄዱት

ብሔራዊ ምርጫዎች ዜጐች ድምፅ በመስጠት መብታቸው ተጠቅመዋል። ያም ሆኖ በወቅቱ የደረሱ እና በጣም አሳሳቢ የሆኑ ክስተቶች ምርጫውን አበላሽተውታል። ሕገ መንግሥቱ ጐልማሶች፣ ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሆነ በሙሉ ድምፅ፣ እንዲሰጡ በመፍቀድ፣ ከጊዜ ወደጊዜ የሚደረጉ ምርጫዎች በሚስጢራዊ ድምፅ አሰጣጥ እንዲሆን ወስኖ፣ ዜጐችም በቀጥታ እና በነፃ በመረጡዋቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት በሕዝብ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ፈቅዶላቸዋል። ሆኖም፣ ገዥው ኢህአዴግ ፓርቲ በግብር በመንግሥት ሥልጣን የበላይነትን ይዟል።

ኢሰመጉ ያሰማራቸው ታዛቢዎች፣ በአገር ወስጥ ያሉ የተመድ ሠራተኞች፣ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እና አገር በቀል መያዶች፣ በዘገቡት መሠረት፣ የ1992 ብሔራዊ ምርጫ እና የ1993 የክልል ምርጫዎች በአብዛኛው አካባቢ በአጠቃላይ ነፃ እና ፍትሐዊ የነበሩ ቢሆንም፣ ግድያን፣ መሰወርን፣ ድምፅ ሰጭዎችን ማስፈራራትን እና ማዋከብን፣ እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማገትን ጨምሮ በተለይ በደቡብ ክልል፣ ከባድና አሳሳቢ ክስተቶች ነበሩ።

በ1992 እና በ1993 ብሔራዊ ምርጫዎች ወቅት ሕገወጥ ድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ማጨቅን፣ በተሰጠ ድምፅ ቆጠራ ማጭበርበርን፣ በጉቦ መደለልን፣ ግድያን፣ ድብድብን፣ የተስፋፋ ማስፈራራትን እና ማዋከብን ጨምሮ ምርጫ የማዛባት ድርጊቶች በገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች መፈጸማቸው ቢገለጽለትም ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተገቢ እርምጃ አለመወሰዱ የገዥው ፓርቲ መሣሪያ ስለሆነ ነው በማለት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሰውታል።

በፈዴራል ፓርሊያሜንት የሕዝባዊ ውክልናን ቁጥር የሚወሰነው እና በሕገ መንግሥቱ የተጠየቀው ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ በዓመቱ ውስጥ ሊደረግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ በገንዘብ እጦት ምክንያት ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፏል። በፈዴራል ፓርሊያሜንት የክልሎች መወከል በ1986 ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ እና 1987 በተደረገው የድምፅ ሰጭዎች ምዝገባ የተመሠረተ በመሆኑ ከፍተኛ መዛነፍ ነበረበት። በ1995 ዓ.ም. የፈዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ደ.ኤታው፣ ቁጥራቸው በ7 ሚሊዮን የሚገመተው የአገሪቱ ዘላን ማኅበረሰቦች ከዴሞክራሲያዊ ውክልና ውጭ መሆናቸው እንደቀጠለ መሆኑን አምነዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ሕተምቤ) ካሉት 548 መቀመጫዎች 496 መቀመጫዎች በገዢው ፓርቲ በኢህአዴግ ወይም ከርሱ ጋር በተዛመዱት ፓርቲዎች ተይዘዋል። ኢህአዴግ እራሱም በትግራውያን ነገድ ስብስብ የበላይነት እንደቀጠለ ነው። ከኢህአዴግ ጋር የተዛመደው ሕወሃት 40 መቀመጫዎችን የያዘ ቢሆንም፣ የፖለቲካ ተዕእኖው ቁጥሮቹ ከሚጠቁሙት በጣም የበለጠ ነው። ኢህአዴግ፣ ተዛማጆቹ፣ እና የኢህአዴግ ደጋፊዎች 108 አባላት ያሉትን የፌዴሬሽን ምክር ቤትን መቀመጫዎች በሙሉ ተቆጣጥረዋል። የዚህ ምክር ቤት አባላት በክልል መንግሥታት እና በፈዴራል መንግሥት የሚሾሙትን የሚመረጡ ናቸው። በደቡብ ክልል ተቃዋሚ አባላት በክልሉ ምክር ቤት 7 ከመቶ ያህል የሚሆኑትን መቀመጫዎች ይዘዋል።

ከመነሻው ለ1993 ታቅዶ የነበረው የሱማሌ ክልል ምርጫ በጥር 16/96 ተካሂዷል። የክልሉ ምርጫ በርካታ መዛባቶች ያጠሉበት እንደነበረ ኢሰመጉ ዘግቧል። ሆኖም፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርደ /ብምቦ/ ክሱን/ስሞታውን ገምግሞ ትክክለኛነቱን አጣጥሏል።

የኢህአዴግ አባልነት ለአባላቱ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ሲሆን፣ ፓርቲው የብዙ የንግድ ሥራዎች ባለቤት እንደመሆኑ ለታማኝ ደጋፊዎቹ ሥራ ሰጥቷል። ከመንግሥት በተጨማሪ ሕወሃት የሬዲዮ ጣቢያዎችን እንዲያንቀሳቅስ ተፈቅዶለታል (ክፍል 2 ሀን ይመልከቱ)።

ዋነኞቹ የፖሊቲካ ፓርቲዎች በሂደት ዘገምተኛ የሆነውን የመጠናከር ሂደት ቀጥለውበታል። በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጎብረት ከተሰባሰቡት 15 ድርጅቶች አንዱ የሆነው፣ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በሰኔ ወር በአገሪቱ ውስጥ የመጀመሪያው የሆነውን ጽሕፈት ቤቱን ከፍቷል።

በነሐሴ ወር ኢህአዴግ ከዚያን ጊዜ በፊት በደፈናው አሻፈረኝ ስላለው አንዳንድ ጉዳዮች መንግሥት ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጎብረት ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸ። ጉዳዮቹም በአባላቱ ስብጥር የተነሳ አሠራሩ አድሎአዊና ወገናዊ ነው የሚለውን አመለካከት ለመቅረፍ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እንደገና ማዋቀር፣ የዜና ማስራጫዎች የዓየር ሰዓት ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች በፍትሐዊነት እንዲከፋፈል ማድረግ፣ በግንቦት 1997 ዓ.ም. ምርጫዎች ላይ ዓ ለምአቀፋዊ ታዛቢዎች እንዲኙ ማድረግ፣ እና በኢ-ፍትሐዊነት ለኢህአዴግ ያደላሉ

ብሎ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዲኃኅ) የሚያምናቸው የምርጫ ሕጐች እንዲሻሻሉ ማድረግ የሚሉትን የመሳሰሉ ናቸው። በጥቅምት ወር ከኢዴኃኅ ጋር ከተገናኘ በኋላ ኢህአዴግ ብዙዎቹን ኢዴኃኅ የጠየቃቸውን እንደ የዜና ማሰራጫዎች የዓየር ሰዓት ማግኘትን እና ዓለምአቀፋዊ ታዛቢዎች መኖርን የመሳሰሉትን ተቀብሏል።

የተመዘገቡ የፖሊቲካ ፓርቲዎች በየሥፍራው የጽሕፈት ቤቶችን ለመክፈት ከክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። በዓመቱ ውስጥ በሙሉ የሥፍራው የመንግሥት ባለሥልጣናት በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ላይ ማካሄድ የቀጠሉት የተስፋፋ ማስፈራራት እና በኃይል መጠቀም ሲላማ እንደነበሩ እንደ መኢአድ እና የኮንሶ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት ያሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘግበዋል። በመኢአድ፣ ሕዳጎ፣ እና በሌሎችም ፓርቲዎች ወይም በጋዜጦች በመቶዎች የሚቆጠሩ ሁኔታዎች ተዘግበዋል። እነዚህም ሁኔታዎች በሲቪክ እንቅስቃሴዎች ላይ ከአካባቢ ሹማምንት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን በአደባባይ ከመሳደብ እስከ ፈንጂ መጣል፣ ቤት ማቃጠል፣ ንብረት መውረስ፣ እና ሰው መግደል ድረስ ነበሩ። በብዙዎቹ በተዘገቡ ድርጊቶች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ማዳበሪያ፣ ሌሎች የግብርና ጥቅሞችን፣ የጤና እንክብካቤ፣ ወይም ሌሎች መንግሥት የሚቆጣጠራቸው ጥቅሞችን ማግኘት ከፈለጉ ከተቃዋሚ ፓርቲዎቹ አባልነት እንዲወጡ ወይም ፓርቲውን እንዲያሳጡ ይጠየቁ ነበር ተብሏል። የፓርቲ ስብሰባዎች ብዙውን ጊዜ ይሰናከሉ ወይም በሕገ-ወጥ አሠራር ይከለከሉ ነበር።

በ1995 ዓ.ም. እና ባለፈው ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት ውስጥ ኢህአዴግ በፋሻ፣ በቶካ፣ በካማሌ፣ በፊጩጫ፣ እና በታራ ውስጥ የነበሩትን የኮሕዴኅ ጽ/ቤቶች መዝጋቱን እና በአባ ሮባ እና በጃርሶ ኮሕዴኅ ዘግቧል። እነዚህም የኢህአዴግ አባላት በተቆጣጠሩዋቸው ምክር ቤቶች ተተክተዋል። የኮሕዴኅ አባላትን እየያዙ ማሠር እና ድብደባዎችም እንደነበሩ ተዘግቧል።

በመኢአድ ዘገባዎች መሠረት በየካቲት 21/1996 ዓ.ም. በአንኮበር በሚኖረው እና የመኢአድ አባል በሆነው በበቀለ ታደሰ ቤት ላይ ድንጋዮች ተወርውረዋል። በየካቲትት 28 ቀን 1996 በአንኮበር ወረዳ የመኢድ አደራጅ ኮሚቲ ሊቀ መንበር በሆነው በዘመድኩን ገብረ ኪዳን ቤት ላይ ቦምብ ተወርውሯል።

በኃይል እንደማይጠቀሙ ካላስታወቁ እና ያለውን መንግሥት ሕጋዊ ባለሥልጣንነት ላልተቀበሉ የፖለቲካ ተሳትፎ እንደተዘጋባቸው ነበር።

በጥቅምት 1994 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትን ምክር ቤት መንግሥት አፍርሶታል። አባላቱም በሙሉ የገዢው ፓርቲ አባላት በሆኑ በጊዜያዊነት ተተክተዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር መሠረት፣ ምክር ቤቱ በፈረሰ በአንድ ዓመት ውስጥ እነዚያን መቀመጫዎች ለመሙላት ምርጫዎች መደረግ ነበረባቸው። በዓመቱ መጨረሻ እነዚህ ምርጫዎች አልተደረጉም።

ሙሰኛነትን የመዋጋት ቀደምት ኃላፊነቱ የፍትሕ ሚኒስቴር ነው። ተመድ ባለው መሠረት፣ ቢሮክራሲያዊ ማዓተት እና ችግሮች ቢኖሩም፣ በአንፃራዊነት ሲታይ ቢሮክራሲያዊ ሙሰኛነት አነስተኛ ነበር። ማኅበራዊ ግፊት፣ ባህላዊ መመዘኛዎች፣ እና ሕጋዊ ቁጥጥሮች ተጣምረው ሙሰኛነትን ለመዋጋት በግብር ላይ ውለዋል። ያም ሆኖ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኃይል ማመንጫ፣ እና የሌሎችም መሠረተ ልማት ጨረታ ተዘውትሮ ሲሰረዝ ግልጽነት አለመኖሩ የሙስና ጥርጣሬዎችን ፈጥሯል። በተጨማሪም፣ በመንግሥት እና በፓርቲ ባለቤትነት የሚካሄዱ የንግድ ሥራዎች መሬት፣ የከተማ ቦታ በሊዝ ለመያዘ እና ብድር ለማግኘት ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው፣ የመንግሥት ሹማምንት የፕራይቬታይዜሽንን ሂደት እንደሚያጠማዝዙት ታምኗል።

የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በ1993 ዓ.ም. ከተቋቋመ በኋላ፣ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እና የመንግሥት ንብረት የሆነውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሥራ አስኪያጆች ጨምሮ፣ ሹማምንትን እና የግል ኑጋዴዎችን ይዞ በሙስናነት ከሷቸዋል። ሆኖም፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የተያዙ ከፍተኛ ሰዎች አልነበሩም። ጉቦ መስጠት ወይም መቀበል ወንጀል ነው።

መንግሥት ሕጉቹ እና ደንቦቹ በሥራ ላይ ከመዋላቸው አስቀድሞ በነጋሪት ጋዜጣ አትሞ ያወጣቸዋል።

ከ19 የሚኒስሮች ምክር ቤት አባላት ወስጥ አንዷ ሴት ነበሩ፣ ሌሎች 2 ሴቶች የሚኒስትር ማዕረግ ነበራቸው፣ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሴቶችም በከፍተኛ የሥራ ደረጀ ላይ ነበሩ። 548 መቀመጫ ባለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ሕተምቤ)

42 ሴቶች፣ 113 አባላት ባሉት የፌዴሬሽን ምክር ቤት 9 ሴቶች ነበሩ። ከጠቅላይ ፍርድ ቤት 14 አባላት 3ቱ ሴቶች ነበሩ።

በነገድ/ጐሣ ፌዴራሊዝም ላይ የተመሠረተው የመንግሥት ፖሊሲ የሁሉም ዋነኛ ነገድ ስብስቦች በሕተምቤ መወከላቸውን ለማረጋገጥ እራሳቸውን የቻሉ የምርጫ ክልሎችን (ኮንስቲቱየንሲስ) መፍጠር አስፈለገ። ያም ሆኖ ትናንሽ የነገድ ስብስቦች በምክር ቤት አልተወከሉም። በ6 ክልላዊ መንግሥታት ውስጥ በምርጫ ክልል መሠረት መቀመጫዎች ለማግኘት ያልመጠኑ 23 የብሔረሰብ ስብስቦች ነበሩ። ሆኖም በ1992 በተደረገው ምርጫ 548 መቀመጫዎች ባሉት ሕተምቤ ከእነዚህ የብሔረሰብ ስብስቦች ግለሰቦች ለ23 ልዩ መቀመጫዎች ተወዳድረዋል።

ክፍል 4 ሰብዓዊ መብቶች ተጥሰዋል የሚለው ውንጀላ በዓለምአቀፋዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ወገኖች ድርጅቶች ስለመመርመሩ መንግሥት ያለው አመለካከት።

የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አገር በቀል እና ዓለምአቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ስብስቦች በመጠነኛ የመንግሥት ቁጥጥር የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን እየመረመሩ ግኝቶቻቸውንም እያተሙ በማውጣት ሲሠሩ ቆይተዋል። በአጠቃላይ መንግሥት አገር በቀል የሆኑትን የሰብዓዊ መብት ስብስቦችን ስለማያምናቸው በጥርጣሬ ይመለከታቸዋል። ሆኖም፣ ከዓለምአቀፋዊ መያዶች ጋር ያለው ግንኙነት በዓመቱ ውስጥ የተሻለ ሆኖ ታይቷል። በጣም ታዋቂ ከሆኑት አገር በቀል የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ሁለቱ ኢሰመጉ እና የኢትዮጵያ ሴቶች የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር (ኢሴሕባማ) ነበሩ። መንግሥት የኢሰመምጉ ዘገባዎች አዘውትሮ በመካድ፣ የፖሊቲካ ድርጅት ነው የሚል መጠሪያ ሰጥቶታል። የሴሕባማ ቀደምት ተግባር ሴቶችን በሕግ መወከል ነው። እነዚህ እና ሌሎች ብዙ ስብስቦች በቅድሚያ የተያያዙት የሲቪክ እና የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት መስጠትን፣ የሕግ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ይህንኑ መሰጠትን፣ እና በፍርድ ቤት የችሎት ሂደትን መከታተል ነው። ሆኖም፣ መንግሥት ከአገር በቀል መያድ ማሕበረሰብ አባላት ጋር ስለሰብዓዊ መብቶች መደፈር መረጃ አይለዋወጥም፣ ወይም ድፍረቶች መኖራቸውን አምኖ አይቀበልም።

ባለፈው ዓመት መባቻ መንግሥት የሰብዓዊ መብቶች ሊግ ከኦነግ ጋር ትስስር አለው የሚለውን ውንጀላ ምርመራውን እንደቀጠለ ነበር። የሊጉ ጽሕፈት ቤቶች እንደተዘጉ